# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 249 የካቲት 14 2005 ገጽ 1


**በተለይም ኢትዮጵያውያን አርበኞች በጠላት ላይ የወሰዱት የማያዳግም እርምጃ ለመድገም እና ኢትዮጵያን ከሀገር ውስጥ ጠላት ከሆነው ህወሃት ለመታደግ፤ ነፃነታችንን አሳልፎ ላለመስጠት፣ ብርቱ ክንዳቸውን በአኩሪ መሰዋእትነት ለማሳረፍ እና ሕያው ምስክር ለመሆን ከተነሱት ከግንቦት 7 ህዝባዊ ሃይል ጋር ሆነን በጋራ በተባበረ ሃይል የምንታገልበት ጊዜ ዛሬ ነው።**

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## በዘንድሮዉ ምርጫ ወያኔ የረጂም ግዜ አጃቢዎቹም ሊከዱት እንደሚችሉ በመነገር ላይ ነዉ ተባለ

በዚህ አመት አጋማሽ ላይ በሚደረገዉ የከተማና የወረዳ ምርጫ የወያኔ አጋር እንደሆኑ የሚነገርላቸውና ከዚህ ቀደም ወያኔን አጅበዉ ምርጫዉን የብዙዎች ምርጫ ያስመሰሉ እንደ ራዕይ፤ ኢፍዴሃግ፤ መኢብንና ቅንጅትን የመሳሰሉ ፓርዎች ዘንድሮ ጭራሽ በምርጫዉ ላይ ላይሳተፉ ይችላሉ የሚል ወሬ አዲስ አበባ ዉስጥ እየነፈሰ መሆኑን ዘጋቢዎቻችን ከአዲስ አበባ በላኩልን ዜና ገለጹ። እነዚህና ሌሎችም የጋራ መድረክ እየተባለ በሚጠራው የፖለቲካ ስብስብ ዉስጥ ተሳታፊ የሆኑ ወደ ዘጠኝ የሚጠጉ ፓርቲዎች ለመጪው ምርጫ ዝግጅት ማድረግ እንዲችሉ ምርጫ ቦርድ የገንዘብ ድጋፍ እንዲደረግላቸው ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት ባለማግኘቱ ቀድሞዉንም ቢሆን ከአጃቢነት ዉጭ ምንም ማድረግ ከማይችሉበት የይስሙላ ምርጫ ሊወጡ እንደሚችሉ የየፓርቲዎቹ መሪዎችና በመናገር ላይ ናቸዉ::

እነዚህ ህዝባዊ ድጋፍና ተቀባይነት የሌላቸዉ ፓርቲዎች በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዕጩዎችን ማቅረብ የግድ በሆነበት በዚህ የአካባቢ ምርጫ የአገሪቱን ሀብት እንደራሱ ንብረት ከሚቆጣጠረዉ ወያኔ ጋር መወዳደር ቀርቶ ለምርጫዉ ከሚያስፈልጋቸዉ የዕጩዎች ቁጥር ዉስጥ ከመቶ አምስቱን እንኳን ማቅረብ አለመቻላቸዉ ታዉቋል። ፓርቲዎቹም ይህንን በሚገባ ስለሚረዱ ምርጫ ቦርድ የገንዘብ እርዳታ እንዲያደርግላቸዉ ለገዢዉ ፓርቲ ለኢህአዴግ አቤቱታ ቢያቀርቡም ኢህአዴግ ጆሮ ዳባ ልበስ ብሎ ጥያቄያቸዉን ሳይሰማ ቀርቷል።

በዚህ የተነሳ አንዳንዶቹ ፓርቲዎች በምርጫዉ ተሳትፈናል ለማለት ብቻ አንዳንድ ቦታ ላይ በጣት የሚቆጠሩ ዕጩዎች ቢያቅርቡም በከፍተኛ የገንዘብ ችግር የተነሳ በምርጫዉ ለመሳተፍ የሚችሉ ባለመሆናቸው የዘንድሮዉን ምርጫ የሚያዘጋጀዉ፤ የሚወዳደረዉና ከራሱ ጋር ተወዳድሮ የሚያሸንፈዉም ወያኔ ብቻ ሊሆን እንደሚችል ከወዲሁ ለማረጋገጥ ችሏል:: ኢትዮጵያ ዉስጥ በምርጫ ቦርድ ተመዝግበው ይንቀሳቀሳሉ ከሚባሉት ከ65 በላይ ፓርቲዎች ውስጥ ሃያ ስምንቱ ከምርጫ በፊት ውይይት ይቅደም ብለዉ ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት ባለማግኘቱ እራሳቸዉን ከምርጫው ማግለላቸው የሚታወቅ ሲሆን ዉሸት የማይሰለቸዉና በኢህአዴግ አባላትና ደጋፊዎች የተሞላው ምርጫ ቦርድ ግን 15 ፓርቲዎች በተወዳዳሪነት ተመዘግብዋል እያለ ህዝብን በማጣለል ላይ መሆን ታዉቋል።

## ሙስሊም ኢትዮጵያውያን ድምጻችን ይሰማ በማለታቸው በፌደራል ፖሊስ አባላት ተደበደቡ

በትናንትናው እለት በተለይም በሻሸመኔ፣ ድሬዳዋ፣ መቱና በርካታ ከተሞች የጁመአን ስግደት ተከትሎ ሙስሊም ኢትዮጵያውያን ድምጻችን ይሰማ በማለት ተቃውሞአቸውን ለመግለጽ ባደረጉት ሙከራ የዘረኛውና አምባገነኑ የወይኔ አገዛዝ የፌደራል ፖሊስ አባላት መደብደባቸውንና በርካቶችም መታሰራቸውን ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ በላከልን ዘገባ ገለጸ።

እንደዘጋቢያችን ሪፖርት ከፍተኛ ተቃውሞ ከታየባቸው ከተሞች መካከል ውስጥ አንዱ በሆነው የሻሸመኔ ከተማ፣ በርካታ ሙስሊሞች በ04 መስጊድ ተገኝተው ድምጻችን ይሰማ መሪዎቻችን ይፈቱ በማለት ተቃውሞአቸውን መግለጻቸውና በተመሳሳይ መልኩም ተቃውሞዎች በበደሌ፣ መቱና ድሬዳዋ መካሄዳቸውን ለማወቅ ተችሎአል።

ዘረኛውና አፋኙ የወያኔ አገዛዝ የሙስሊሞችን ተቃውሞ ለማስቆም ድብደባና እስራትን የጨመረ የተለያዩ ሙከራዎችን ቢያደርግም ተቃውሞው ከአዲስ አበባ ውጭ አድማሱን እየተስፋፋ ከመሄድ በስተቀር የመቀነስ ሁኔታ ሊታይ አለመቻሉን ዘጋቢያችን በላከው ሪፖርት አክሎ ገልጹአል።

በተያያዘ ዜና ሰሞኑን በተለያዩ የተቃዋሚ ሃይሎች ድረ ገጾች ላይ እንደተዘገበው በአሜሪካ የሞኖሩ ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች በዛሬው እለት በዋይት ሀውስ ፊት ለፊት ታላቅ የተቃውሞ ሰልፍ እንደሚያደርጉ ታውቁአል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ግዜ

## ዘረፋ የአምባገነኑ ወያኔ አገዛዝ ባለስልጣናትና አገልጋዮቻቸው የወቅቱ ቀዳሚ ተግባር እየሆነ ነው ተባለ

ላለፉት ሃያ አንድ አመታት በኢትዮጵያዊያን ጫንቃ ላይ ተፈናጠው ያለምንም ረፍትና ሃፍረት ህዝብን እየዘረፉ የሚገኙት የዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ባለስልጣናትና አጫፋሪዎቻቸው ዝርፊያውን በተባባሰ መልኩ እየቀጠሉበት መሆኑን ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ ባስተላለፈልን ዘገባ አመለከተ። እንደዘጋቢያችን ሪፖርት ባሁኑ ሰአት ኢትዮጵያ ውስጥ እየታየ ያለው ዘረፋ ከከፍተኛ ባለስልጣናት አልፎና ወደታችም በስፋት በመውረድ ቀደም ብሎ በድብቅ ይካሄድ የነበረው ዘረፋ በተባባሰ መልኩና ለህዝብም ግልጽ በሆነ መንገድ እየታየ መምጣቱ ታውቋል።

ዘጋቢያችን ባስተላለፈልን ሪፖርት ሰሞኑን በኦሮሚያ በየዓመቱ በሚከበረው ለአባ ገዳ ስርአት ላይ ከህዝብ የተሰበሰበውን ገንዘብ በአካባቢው የሚገኙ የወያኔ ባለስልጣናት መቀራመታቸው ታውቋል። ቀደም ብሎ እንደሚታወቀው በጉጂ ኦሮሞ ባህል አንድ አባገዳ ስልጣን በተረከበ በስድስተኛው አመት ጉማታ ወይም ስጦታ ከህዝቡ የሚሰበስብ ሲሆን ስልጣኑን የሚያስረክበው ደግሞ በስምንተኛው አመት በመሆኑ፣ ለሁለት አመታት የሚሰራበትን ገንዘብ፣ እህል ወይም የቤት እንስሳ ከህዝቡ በስጦታ መልክ ይቀበላል።

ይሁን እንጂ በዚህ አመት አባገዳው ጉማታውን ለመሰብሰብ ዝግጅት በሚጀምርበት ጊዜ የቦረና ዞን የወያኔ አገዛዝ ግልገሎች ከአሁን በሁዋላ ጉማታው መሰብሰብ ያለበት በመንግስት ነው በሚል ሽፋን የጉማታ ሰብሳቢዎች በተለያዩ አካባቢዎች መዋቀራቸውና የወያኔ ሆድ አደር ባለስልጣናቱም ከህብረተሰቡ እየዞሩ በአባገዳው ስም የሰበሰቡትን እጅግ በርካታ ገንዘብ ፣ ለአባገዳው ሳይሰጡ የተወሰነውን ለበላይ አለቆቻቸው የተወሰነውን ለራሳቸው ማድረጋቸውን፣ ዘጋቢያችን የአካባቢዉን ነዋሪዎች ዋቢ በማድረግ በላልከልን ዘገባ ላይ አመልክቷል።

ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ወደስልጣን ወምበር ከመጣበትና ከመምጣቱም በፊት ባሉት ጥቂት የማይባሉ አመታት ውስጥ አልጠግብ ባይ የወያኔ ሆዳሞች በዝርፊያ ስራ ተጠምደው እንደሚገኙ በስፋት ሲዘገብ እንደቆየ ይታወሳል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ፋሺስት ጣሊያን ወታደሮች የኢትዮጵያን ህዝብ የጨፈጨፉበት 76ኛ አመት ታስቦ ዋለ

የወራሪዉ ፋሽስት ጣሊያን ወታደሮች አዲስ አበባ ዉስጥ በአንድ ጀምበር ከ30ሺ በላይ ሠላማዊ ዜጎችን የጨፈጨፉበት የሰማዕታት ቀን ከትናንት በስቲያ ማክሸኞ አዲስ አበባን ጨምሮ በአለም ዙሪያ ኢትዮጵያዉያን በሚኖሩባቸዉ አካባቢዎች ሁሉ ታስቦ ዋለ። የእናት አገራቸዉ በጠላት መወረር ያንገበገባቸዉ ጀግኖቹ አብርሃም ደቦጭና ሞገስ አስገዶም በወቅቱ አዲስ አበባ ዉስጥ የሙሶሊኒ ተጠሪ በነበረዉ በማርሻል ግራዚያኒ ላይ ያደረጉትን የግድያ ሙከራ ለመበቀል የፋሺስት ጣሊያን ወታደሮች በወሰዱት አረመኔያዊ እርምጃ ከ30ሺ በላይ ወንዶች፤ ሴቶች፤ ህጻናትና አረጋዉያንን ያለ ርህራሄ መጨፍጨፋቸዉ ይታወሳል። ይህ በየአመቱ ዬካቲት 12 ቀን "የሰማዕታት ቀን" እየተባለ ታስቦ የሚዉለዉ በአል ዘንድሮም ለ76 ግዜ በመላዉ ኢትዮጵያ ዉስጥ በኃዘን ስሜት ታስቦ የዋለ መሆኑን አዲስ አበባና በየክልሉ የሚገኙት ዘጋቢዎቻችን በላኩልን ዜና ገልጸዋል።

በቀዳማዊ ኃ/ስላሤና በደርግ ዘመነ መንግስት የአገሪቱ ርዕሰ ብሔርና ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣኖች በተገኙበት በዬካቲት 12 አደባባይ በታላቅ ስነስርአት ተከብሮ በሚዉለዉ የሰማዕታት ቀን በዚህ አመት ተገኝቶ በጀግኖች ሐዉልት ስር የአበባ ጉንጉን ያኖረዉ የራሱ መስሪያ ቤት ሠራተኞች እንኳን በስም ለይተዉ የማያዉቁት የአዲስ አበባ ከተማ ምክትል ከንቲባ አባተ ስጦታዉ የተባለ ሰዉ እንደሆነ ዘጋቢዎቻችን አክለዉ የላኩልን ዜና ያስረዳል። የዘንድሮዉን የሰማዕታት ቀን አከባበር ከወትሮዉ ለየት የሚያደርገዉ የአትዮጵያ ህዝብ በተለይ ከኢትዮጵያ ዉጭ በትላልቆቹ የአለም ከተሞች ዉስጥ የሚኖረዉ ኢትዮጵያዊ ኢጣሊያ ዉስጥ ጨካኙን የፋሺስት ጦር መሪ ማርሻል ግራዚያኒን ለመዘከር የተሰራዉን የመታሰቢያ ቦታ በመቃወም ጣሊያን ኤምባሲ ፊት ከፍተኛ የተቃዉሞ ሠልፍ ሲያደርጉ መዋላቸዉ ነዉ።

የዘንድሮዉ የሰማዕታት ቀን ከኢትዮጵያ ዉጭ ለንደን፤ ፓሪስ፤ ቶሮንቶ፤ ዋሺንግተን ዲሲ፤ ፍርንክፈርት፤ ሙኒክ ፤ አመስተርዳምና ሲዲኒ አዉስትራሊያ ዉስጥ በከፍተኛ ድምቀት ተከብሮ መዋሉን በየከተሞቹ የሚገኙት ዘጋቢዎቻችን በላኩልን ዜና ገልጸዋል። በየከተማዎቹ በተካሄደዉ የበአሉ (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## የካቲትን የምንዘክረው ከሀገር በቀል ወራሪው ህወሃት ጋር በመፋለም ነው!!

ቀደምቶቻችንን የምናስታውስበት፣ ሀገራችንን ከጠላት ወራሪ እና አንድነቷን ለማስጠበቅ ያደረጉትን ተጋድሎ ከምንዘክርበት እለት አንዱ የካቲት 12 ነው። በዚህ ግዜ ይህንን ታሪክ ገልብጦ ለማበላሸትና ለመጻፍ የሚጥረውን፣ የአሁኑን የግራዚያኒ ትንሽ ወንድም ሀገር በቀል ዘረኛ መንግስት የሆነውን ህወሃት/ ኢህአዴግን ህይማኖት፣ ዘርና ጾታ ሳይለየን የምንታገልበት ሁነኛ ወቅት ላይ እንገኛለን።

የቀድሞዋ የአፍሪካ ሀገራት የነጻነት ተምሳሌት የሆነችው እማማ ኢትዮጵያ፤ ዛሬ ሀገር በቀል በሆኑ የዘረኛ መዥገሮች ስብስብ ተጣብቃ የአበው መሰዋእትነት ከንቱ ይሆን ዘንድ ወያኔዎች እየሰሩ ነው። ጥንታዊ ታሪኳን በመፋቅ፣ ባልተደረገና ባልተፈጸመ ታሪክ ለመተካት ወያኔ/ኢህአዴግ እያንዳንዱን የአበውን የታሪክ ማህደር በማጥፋት፣ እንደ አቡነ ጴጥሮስ የመሳሰሉ የጀግኖችን ሀውልት አሻራ በማፍራረስ ርካሽ የሆነ ግዚያዊ የፖለቲካ ጥቅም ማስገኛ ስራ ላይ በመሰማራት ሀገራችንን ወደኋለዮሽ እድገት እየጎተቷት ይገኛሉ።

ሁለቱን ገዳዮች የሚያገናኛቸው፤ የግራዚያኒ ወታደር አበው ለነጻነታቸው ለአንድነታቸው ሲያደርጉት የነበረውን ተጋድሎ ለማስቆም፤ የህዝቡን የትግል ሞራል ለመግደል የአዲስ አበባን ነዋሪ ቁጥሩ 30ሺ የሚሆን ንጹሃን ዜጎችን በመጨፍጨፍ ፋሽስትነቱን ለማሳየት ያደረገው ያልተሳካ ሙከራ ነው፡፡ ይሁን እንጅ ኢትዮጵያውያን ለነጻነታቸው የሚያደርጉትን ትግል ይህ አልገታቸውም። በተመሳሳይ ደግሞ ዘመን አመጣሹ የየካቲት አስራ አንዱ ወያኔም፤ እንደፋሽስቱ ሁሉ በንጹሃን ህዝባችን ላይ በጎንደር ስላሴ፣ በምርጫ 97፣ በጋምቤላ፣ በአዲስ አበባ፣ በኦሮምያ፣ በአዋሳ፣ በሀረር አሁን ደግሞ በሙስሊሙ ወገናችን ያደረሰው ጭፍጨፋ፣ እስርና ግድያ ከግራዚያኒ ጋር ያመሳስለዋል። ልዩነታቸው ይሄኛው ሀገር በቀል ወራሪ መሆኑ ነው። ምን አልባትም ወያኔ ልደቴ ብሎ የሚጨፍርበት የካቲት 11 ለሱ የድል ቀን ሲሆን፤ ለእኛ ደግሞ አባቶቻችን የምናስታውስበት የመከራ ቀን ነው።

በየካቲት12 የኢትዮጵያ ህዝብ ለነጻነቱ፣ ለአንድነቱ፣ ለሀገሪቱ ክብር የፋሽስቱን ወራሪ ሃይል በመመከት፤ ልጅ አዋቂ ሳይለይ ከሁሉም የሀገሪቱ አቅጣጫዎች በመጉረፍ ጠላትን በማስጨነቅ እየሞቱም አልበገርነታቸውን ያስመሰከሩበት ልዩ ቀን ነው። ኢትዮጵያ ብቸኛዋ የአፍሪካ የነጻነት ተምሳሌት ሀገር እንድትሆንም በማድረግ፤ ወርሃ የካቲት ታሪካዊ ወርና በድል አጥቢያነት በሀገራችን እንዲሁም በአሁጉራችን አፍሪካ ዘለአለም እንዲታወስና እንዲዘከር አድርገው አበው አልፈዋል። ይህን የማስጠበቅ ታሪካዊ የሞራል ግዴታ የማን ነው?

አበው የፋሽስቱን የግራዚያኒ ወራሪ ጦር ድባቅ በመምታት አይቀጡ ቅጣት በመቅጣት ሀገራችንን ከጠላት ወራሪ አድነው አስረክበውናል። በዚህ ታሪካዊ ገድል በሆነው በወርሃ የካቲት የተሰዉት ጀግኖች፣ የኢትዮጵያ ልጆች አጥንትና ደም መሰዋእትነት ከቶ ከታሪክ ማህደር የማይጠፋ ስማቸው ከመቃብር በላይ ሆኖ ሲዘከር ይኖራል። ይህ ትውልድ ይህን የማስጠበቅ የታሪክ ባለተራ ነው እንላለን።

ግንቦት 7፣ የአባቶቻችንን ጀግንነትና ወደር የሌለውን የሀገር ፍቅር፣ የሀገር ክብር፣ የቁርጠኝነት መንፈስና የአደረጉት መሰዋእትነት ከንቱ ሆኖ እንዳይቀር ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይል ይታገላል። በቁርጥ ቀን ልጆች በቁርጥ ቀን ሰዓትም ለመድረስ፤ እስከመጨረሻው በመታገል ታሪካዊ ግዴታውን ለመወጣትና ይህን ድል ለማስመለስ፤ አስመልሶ ለትውልድ ለማስረከብ፣ ለማስጠበቅ እያንዳንዷን ደቂቃ ሊጠቀምባት ቆርቶ ተነስቷል።እርሰዎስ?

የሀገራችን ህዝብ ሆይ፡- የኢትዮጵያ ጀግኖች እነ አጼ ሚኒሊክ፣ የበላይ ዘለቀ፣ እነ አብዲሳጋ፣ እነ ዘራይደረስ፣ እነ አቡነ ጴጥሮስ፣ እነ አፄ ዮሃንስ፣ እንደ ቋራው ካሳ እና ሌሎችም በበቀሉበት፣ በተፈጠሩበት በጥቁር አፈር ምድር፤ ፀረ-ኢትዮጵያ ሀገር በቀል ዘረኛ ሃይሎች መፈጠራቸው አሳዛኝ ታሪክ መሆኑን እኛም እንመሰክራልን። ይሁን እንጅ፣ ቅሉ ይህንን በሁለት ትውልድ መካከል የተፈጠረውን የሰማይና የምድር ልዩነት ቁጭ ብለን በማየት ከንፈራችንን እየመጠጥን የምንቀመጥበት ሰአት ላይ አይደለንም። ጥሪ ከወዲያ ማዶ እየተበራከተ ነው። የድረሱልን ጥሪ!

ስለዚህም መላው የሀገራችን ህዝብ ወያኔን ለማስገደድ አሊያም ለማስወገድ አቅሙ በፈቀደ ሁሉ በገንዘብ፣ በእውቀት በጊዜና ጉልበቱ በመርዳት ታግለን የካቲትን የመሰዋእትነት መንፈስ እያስታወስን፣ ግንቦት 7ን የህዝብ ድምጽ ለማስከበር ይህ ትውልድ ሞራላዊ ግዴታ አለበት እና እንነሳ! እንሂድ።

በአንጻሩ በወያኔ መንደር በአጋጣሚም ሆነ በጥቅም ምክንያት ያላችሁ፡- እንደ ጠዋት ጤዛ ብን ብለው ከሚጠፉ አምባገነኖች ጋር በመለጠፍ ህዝባችንና ሀገራችንን መበድልና ማሰቃየት ለታሪክ ተጠያቂነት ይደርጋል። በወንጀል ተባባሪነት ስለሚያስጠይቅ ከወዲሁ መንገድን በማስተካከል እምቢ ለህወሃት፣ በቃኝ ባርነት፤ በሚል የህዝብ አጋርነትና ድጋፍ ወደ አለው የነጻነት ትግል በመቀላቀል ከማይሻር፣ ከማይጠፋ የታሪክ ማህደር ውስጥ ራስዎትን ያስገቡ ዘንድ የካቲት ጥሩ አጋጣሚ ነው።

በተለይም ኢትዮጵያውያን አርበኞች በጠላት ላይ የወሰዱት የማያዳግም እርምጃ ለመድገም እና ኢትዮጵያን ከሀገር ውስጥ ጠላት ከሆነው ህወሃት ለመታደግ፤ ነፃነታችንን አሳልፎ ላለመስጠት፣ ብርቱ ክንዳቸውን በአኩሪ መሰዋእትነት ለማሳረፍ እና ሕያው ምስክር ለመሆን ከተነሱት ከግንቦት 7 ህዝባዊ ሃይል ጋር ሆነን በጋራ በተባበረ ሃይል የምንታገልበት ጊዜ ዛሬ ነው።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!**

## ሙስሊም ኢትዮጵያውያን ድምጻችን ይሰማ በማለታቸው በፌደራል ፖሊስ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ድምፃችን ይሰማ ዋሺንግተን ዲሲ እንዳስታወቀው፤ ሰልፉ የተዘጋጀው የዘረኛው የወያኔ አገዛዝ በሙስሊሞች ላይ እየፈጸመ ያለውን የሰብዓዊ መብት ጥሰት ለማውገዝና ረዥም ጊዜ ላስቆጠረው የኢትዮጵያ ሙስሊሞች የመብት ትግል አጋርነትን ለመግለጽ ነው።

የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ላነሱት የመብት ጥያቄ የወያኔ አፋኝ ስርአት ቀና ምላሽ ለመስጠት ፈቃደኛ ካለመሆኑም በላይ ህግን በሚፃረር ሁኔታ በመብት ጠያቂዎቹ ላይ መጠነ ሰፊ የሰብዓዊ መብት ጥሰት መፈጸሙን የጠቆመው ድምፃችን ይሰማ፤ ከዚያም አልፎ በሙስሊሙ መሪዎች ላይ የእስር፣የግርፋትና የማንገላታት ድርጊት መፈፀሙን አመልክቷል።

ድምጻችን ይሰማ ዋሽንግተን ዲሲ አምነስቲ ኢንተርናሽናል፤ እንደ ፈረንጆቹ አቆጣጠር ከሐምሌ 12 ጀምሮ 17 ዋነኛ የሙስሊሙን ሰላማዊ ትግል መሪዎችን ጨምሮ በርካታዎች እንደታሰሩ፣ እንደተገረፉ እና እንደተሰቃዩ ሪፖርት ማውጣቱን አስታውሷል። አያይዞም የኢትዮጵያ ሙስሊሞችና በእስር ላይ የሚገኙት መሪዎቻቸው በፖለቲካ ተጽጽኖ ስር ከወደቀ ፍርድ ቤት ፍትህን ሊያገኙ ይችላሉ ተብሎ ፈጽሞ እንደማይጠበቅ ዓለማቀፉ ማህበረሰብና ለጋሽ ሀገራት ሊያውቁት እንደሚገባም ድምፃችን ይሰማ ዲሲ ጠቁሟል። በመሆኑም የ ወያኔው ዘረኛ አገዛዝ በኢትዮጵያዊያን ላይ እየፈጸመ ያለው የመብት ጥሰትና ወንጀል እጅግ ሳይዘገይ በዓለማቀፉ ማህበረሰብ ዘንድ ትኩረት ያገኝ ዘንድ ኮሚቴው ጠይቋል።

የኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታይ የሆኑ ወንድሞቻችንም በወያኔው አገዛዝ የተለያዩ አፋኝ ፖሊሲዎችና አሠራሮች ተጠቂ መሆናቸውን እንደሚገነዘቡ የጠቀሰው የድምፃችን ይሰማ ዲሲ መግለጫ፤በመሆኑም ክርስቲያን ወንድሞቻቸው ዛሬ በዋይት ሀውስ ፊት ለፊት ሙስሊሞች በሚያካሂዱት የተቃውሞ ሰልፍ ላይ አብረው እንዲሳተፉ ጥሪ አቅርቧል።

ይህ በንዲህ እንዳለ የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ(ሰመጉ) በቅርቡ "ጅሃዳዊ ሃረካት" በሚል ርዕስ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የተላለፈው ዘጋቢ ፊልም የተከሰሱ ሰዎችን ሕገመንግስታዊ መብት የጣሰ ነው ሲል በትናንትናው ዕለት ባወጣው መግለጫ አስታወቀ፡፡

ሰመጉ በዚሁ መግለጫው በፌዴራል ፖሊስና በብሄራዊ ደህንነት እና ጸጥታ ባለስልጣን ተዘጋጅቶ በኢቲቪ እንዲቀርብ የተደረገው ፊልም ተጠርጣሪዎቹ በሕገመንግስቱ መሰረት በተከሰሱበት ወንጀል ከፍርድ በፊት እንደጥፋተኛ ያለመቆጠር መብታቸውን የጣሰ መሆኑን ጠቁሞ ይህ በመሆኑም ከአሁን በኋላ ተከሳሾቹ ለፍርድ ቤት የመከላከያ ምስክሮችን የማቅረብ አቅማቸው አስቸጋሪ እንዳደረገው ጠቅሶአል፡፡

የፌደራል ፖሊስ እና የብሄራዊ ደህንነት እና ጸጥታ ባለስልጣን እንደ ህገመንግስት ተቋምነታቸው በአሁኑ ሰአት በፍትህ ሚኒስቴር የፌደራል ማእከል አቃቢ ህግ በነዚህ ተጠርጣሪዎች ላይ በከፈተው የሽብርተኝነት ወንጀል ክስ በምርምራ ያገኙትን ማስረጃ እንደሚያቀርቡ ቢጠበቅም፣ ተቋማቱ በህገመንግስቱ አንቀጽ 20 የተደነገገውን ዜጎች ፍርድ ቤት የመጨረሻ ውሳኔ እስከሚሰጥ እንደጥፋተኛ ያለመቆጠር መብታቸውን በመጣስ ፣ ተከሳሾች ወንጀል ስለመፈጸማቸው አውጅዋል ሲል አስታውሷል።

ዘጋቢ ፊልሙ ፍርድ ቤቶች በህዝብ ዘንድ ያላቸውን ተቀባይነት የሚያዛባ ይሆናል ያለው ሰመጉ፣ የሰብአዊ መብቶች ጉባኤ በወያኔ አገዛዝ በኩል የተወሰደውን ድርጊት ከማውገዝ ባተጨማሪ ዘጋቢ ፊልሙን ያዘጋጁት እና እንዲሰራጭ ያደረገው የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን እና ራዲዮ ድርጅት ከድርጊታቸው እንዲቆጠቡና የሚመለከተው አካልም ድርጊቱን በማውገዝ አስፈላጊውን ማስተካከያ እንዲያደርግ ጠይቋል።

# የህወሃት መሪዎች "የኢትዮጵያ ታሪክ እንደገና መፃፍ አለበት!" ይላሉ:: ለምን??

(ከገብረመድህን አርአያ ክፍል 2)

ወያኔ ታሪክን ልክ እንደ አዲስ ከዜሮ ከሃዲው መለስ እና ሌሎች የወያኔ ጀሌዎችን ጀግና ነገር ግን ስለ እውነት እና ነጻነት ሲሉ የተዋደቁ እና የተሰዉ ሰማእት አባቶቻችንን ደግሞ ፈሪ እና ከሃዲ አድርጎ የመጻፍ ዘመቻውን ወያኔ ከሚቆጣጠራቸው መገናኛ ብዙሃን እና አሁን አሁን በብዛት እየተጻፉ ከሚወጡ እርባና ቢስ መጻህፍት መረዳት ይቻላል::

ወያኔ በኢትዮጵያ የብሄር ብሄረሰብ መብት አምጥቼያለሁ ይለናል:: ውሸት! የሆነው እናእየሆነ ያለው አገሪቷን በዘር ከፋፍሎ ሲያበቃ እነኚሁ መብት አምጥቼላቸኋለሁ የሚላቸው ብሄሮች የዘር ማጥፋት ዘመቻውን እያካሄደባቸው ይገኛል::

ወያኔ ግዙፉን የደርግ ሰራዊት ደምስሼ ኢትዮጵያን ነጻ አውጥቻለሁ ይለናል:: ቅጥፈት!! የሆነው እና እውነታው ሌላ ነው:: ትክክለኛ የታሪክ ተንታኝ ከአንድ ብሄር በተውጣጣ እና በአብዛኛው ዜጎችን የማይወክል ይልቁንም ታሪካቸውን የሚሰድብ እና የሚያንቋሽሽ ፖለቲካ ይዞ በመጣ የመርዘኞች ቡድን የኢትዮጵያ ጦር ተሸነፈ ብሎ መቀበል ፍጹም ስህተት ይሆናል:: ለኢትዮጵያ ጦር መሸነፍ በወቅቱ የነበረው የከሰረ የኮሚኒስት ስርዓት መላሸቅ እና የፖለቲካ ስርዓቱ ከቀዝቃዛው ጦርነት መዳከም ጋር ተባብሮ የእዝ ሰንሰለቱ በመላላቱ ያስከተለው የመዋጋት መንፈስ መቀዝቀዝ አይነተኛ እና ወሳኙን ሚና ተጫውቷል::አንዳንዶች በወቅቱ በወያኔ መሪዎች የተሰጠውን ቃል አምነው ለጊዜውም ቢሆን እስቲ እንያቸው በሚል ካሳደሩት ዛሬ ላይ እንደ ታላቅ ስህተት ሊቆጠር የሚችል የፖለቲካ ስሌት ስህተት በቀር ብዙሃኑ የኢትዮጵያ ህዝብ እንኳን ወያኔን መጣብን እንጂ መጣልን ብሎትም አያውቅ::

ሌላው የወያኔ አይን ያወጣ የታሪክ ሽምጠጣ አንድ አንዶች ህገ አራዊት ብለው የሚጠሩት እና ሟቹ እኩይ መለስ ዜናዊ እንደ ማወናበጃ የሚጠቀምበት ህገመንግስት ነው:: ወያኔ ሲዘብት ለኢትዮጵያ ህዝብ አስደናቂ እና ነጻነቱን ያጎናጸፈ ህገመንግስት አመጣን ይለናል:: ሓሰት!! ህገ መንግስቱበውስጥ ከያዛቸው አንቀጾች በመለስ አላማው ምን እንደሆነ እነሆ ከረቀቀበት የዘጠናዎቹ አጋማሽ ጀምሮ ምን ማለት እንደሆነ የኢትዮጵያ ህዝብ እየኖረበት አይቶታል እና ዝርዝር ማብራሪያ ውስጥ መግባት አያሻኝም::

ሲመጻደቅ ደግሞ ኢትዮጵያን ከመበታተን አዳናት ይለናል:: ክህደት!! ስብሓት ነጋሲያዳልጠው ኢትዮጵያን አፍርሰን እንደ አዲስ እየሰራናት ነው ይልና ማን አፍራሽ እና በታኝ እንደሆነ ሳያውቀው ይነግረናል:: ወያኔ እንዳሰበው ሳይሆን እንደ ኢትዮጵያ ህዝብ ጽናት እና እምነት አገራችን እስካሁን በአንድነት ቆይታለች:: ይብላኝላቸው ለእነሱ እንጂ ከወያኔ ውድቀት እና ሞት በኋላም አንድነቷን ጠብቃ ትቀጥላለች::

ሲላቸው ደግሞ የአክሱም ታሪክ የጥቂት የትግራይ አካባቢዎች ታሪክ ነው ይሉናል:: ሙሉውን ትግራይ እንኳን አያጠቃልልም ሲሉም በድፍረት ይነግሩናል:: ጉድ ነው!! ምን አይነትማህጸን ይሆን እንደዚህ አይነት ከሃዲዎችን የወለደች?? በአንድ አገር ታሪክ ውስጥ አይነቱ ይለያይ እንጂ በታሪክ አጋጣሚ አሁን በማሊ እንደምናያቸው እና እንደአፍጋኒስታኑ ታሊባን አይነት ከተጠማዘዘ የሃይማኖት ፍልስፍና ተነስተው አገራዊ ጥፋት የሚያደርሱ ቡድኖች ስልጣን ሊይዙ ይችላሉ:: እንደ ወያኔ አይነት ግን ከአንድ አካባቢ ተቧድነው መጥተው በዚህ የመረጃ እና የእውቀት ዘመን ለክህደት እና ለጥፋት የሚተጉ ቡድን ግን አንብቤም ሆነ ሰምቼአላውቅም:: የአክሱም ታሪክ የመላው ኢትዮጵያውያን ታሪክ ነው:: እንደዘመኑ እና ጊዜው የተፈጸሙ ታሪኮች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ሁሉንም የአካባቢውን ማህበረሰቦች መንካታቸው እስካልቀረ ድረስ ታሪኩ ሁሉም ኢትዮጵያዊያን ሊኮሩበት ሊወያዩበት እና ሊማሩበት የሚገባ የጋራ ታሪክ ነው:: ህዝባዊ ወያነ በኢትዮጵያ ላይ ያደረሰው ጥቃት እንደ ዮዲት ጉዲት እና አህመድ ግራኝ በአጭር ጊዜ ባይሆንም ላለፉት አርባ አመታት ገደማ ከበረሃ ጀምሮ በኢትዮጵያዊነት ስነ ልቦና እና ቅርስ ላይ ያደረገውን ጥቃት ስናይ ሁለቱ ካደረሱት መጠነ ሰፊ ጥቃት ጉዳቱ ይበልጥ እንጂ አያንስም::

የህወሃት ጥንሥሥ የጀመረው በ1964 በቀ.ኃ.ሥ ዩኒቨርሲቲ በሻዕቢያ "ጥሩምቡሌነት" ("ጥሩምቡሌ" ማለት በቀድሞ አነጋገር በገንዘብ የተገዛ ቅጥረኛ ባንዳ እንደ ማለት ነው::) በተሰባሰቡ የትግራይ ዘረኞች ነበር:: ሻዕቢያ ለራሱ እኩይ ተልዕኮ ማስፈጸሚያ ይረዳው ዘንድ ጥቂት ዘረኞችን ሰብስቦ ገንዘብ ፈሰስ በማድረግ ማህበረ ገስገስቲ ብሄረ ትግራይን ፈጠረ:: የድርጅቱን ከጥንስሡኢትዮጵያን ለማጥፋት መነሳት የኔን ምስክርነት ማንበቡ ብቻ በቂ አይሆንም:: በአንድ አንድ ድረ ገጾች ላይ እና በኢንተርኔት በቀላሉ ሊገኝ የሚችለውን የድርጅቱን የ1968 ፕሮግራም ማየቱ ብቻ በቂ ነው::

ህወሃት በቀላሉ ሊደልዛቸው እና ሊያጠፋቸው የማይችላቸውን ከፍተኛ የአገር ክህደት እና የጅምላ ግድያ ወንጀሎችን የግል መዛግብቶቼን አመሳክሬ እዘረዝራለሁኝ:: አንባቢያን ዝርዝሩ ያለቅደም ተከተል መቀመጡን ልብ ይበሉ፤

1.ገና ከመመስረቱ ብዙም እድሜ ሳያስቆጥር በ1968 ንጹሃን የትግራይ ልጆችን ሲለው ኢዲዩ ሲያሰኘው ደግሞ በኢህአፓ እና በደርግነት እየወነጀለ በጅምላ ፈጃቸው:: አባወራ እና እማወራዎችን በመግደል ብቻም አላበቃም:: የብዙሃንንም ንብረት በመውረስ ቀሪ ቤተሰባቸውንም ጭምር ነው አይቀጡ ቅጣት የቀጣው:: ብዙሃን ህጻናትንም ያለወላጅ ፤አረጋዊያንንም ያለጧሪ እና ቀባሪ አስቀራቸው:: ይህ በትግራይ በስፋት የሚታወቅ ሃቅ በመሆኑ በዘመኑ የወያነ ጉጅሌ ጦር ይንቀሳቀስ በነበረባቸው ቦታዎች ይኖሩ የነበሩ ሰዎችን በመጠየቅ ማንም ሊረዳው የሚችለው ሃቅ ነው::

2.በወርሃ ህዳር1969 ዓ.ም. ከህወሃት አመራር ተወክለው መለስ ዜናዊ እና አባይ ጸሃየ ከሻዕቢያ ጋር አሁን አወዛጋቢ ተብለው የሚነገርላቸውን ከባድመ ጀምሮ እስከ የአፋር አካባቢዎች ድረስ ያሉ ቦታዎችን አሳልፈው የሰጡ መሆናቸው እና ከብዙ አመታት በኋላም ይህንኑ መዘዝ ተከትሎ በተነሳ ጦርነት ከመቶ ሺህ በላይ ኢትዮጵያውያን በጦርነት ያለቁበት ሁኔታ እና የጉዳዩም እስከአሁን ሳይቋጭ በእንጥልጥል መቆየት ማንም ሊዘነጋው የማይገባው ሃቅ ነው:: ህወሃት ይህንን አገር የመሸጥ ስራውን ይሰራ የነበረው ገና በደፈጣ ውጊያ ላይ በነበረበት ጊዜ እና በትግራይ ህዝብ ጭምር ምንም አይነት ተቀባይነትም ሆነ ውክልና ሳይኖረው መሆኑ ልብ ሊባል ይገባል::

3.በ1968 ዓ.ም. ጀምሮ በተለያዩ አጋጣሚዎች ህንፍሽፍሽ ተነሳ በማለት አመራሩ የተምቤን: እንደርታ: አዲግራት: ክልተ አውላሎ: ራያ: በትንሹም ቢሆን በአክሱም እና አድዋ ከነበሩ ታጋዮች ውስጥ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ገድለዋል:: ለዚሁም ምስክርአሁን በህይወት ያሉ ታጋዮች እና ህዝቡ እማኝ ነው:: በየአካባቢውም ማስረጃ ሊሆኑ የሚችሉ የጅምላ መቃብሮችን ጭምር ማሳየት ይቻላል::

4.በ1969 በወርሃህዳር በወልቃይት ጠገዴ : ዳንሻ: ጠለምት: ሁመራ: እንዲሁም ከወሎ አካባቢውን ከተወላጆች በማጽዳት የትግራይ መሬት ነው በማለት በካርታ ቀላቅሎ አስታወቀ::

5.በ1971 ዓ.ም. የህወሃት አንደኛ ጉባዔ አንስቶ የድርጅቱ አመራር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያንን የአማራው ገዢ መሳሪያ ነች በማለት የጥቃት በትሩን መዘርጋቱን ተያያዘው:: ይህ እኩይ ትንተናው ከኮሚኒስታዊ የፖለቲካ ፍልስፍናው ጋር ተጣምሮ በፈጠረው የተወላገደ ስነልቦና እየተመራ በብዙ አብያት ክርስቲያናት ላይ እና ገዳማት ላይ የዘረፋ እና የጥቃት እጁን ሰነዘረ:: ለዘመናት የኖሩ የሃይማኖቱን ትውፊት እና ባህላዊ እሴቶችን ማህበረሰቡን በማስገደድ ከለከለ:: ክርስትና ማንሳት እና ሰርግ ማድረግን ጭምር:: ቀሳውስትን በግልጽ ማጥቃት እና ቤተ እምነቶችንም ማርከስ እና መዝረፍ የሰርክ ግብሩ አደረገው::

6.በ1972 ጥቅምትወር ጀምሮ በወልቃይት ጠገዴ ህዝብ ላይ የወያነ ህወሃት የዘር ማጽዳት ስራ አማራ ጸረ ትግራይ ነው በሚል ይፋዊ መፈክር ታጅቦ ከህጻን እስከ ሽማግሌ ድረስ ተፈጸመባቸው:: ቤተሰቦች መኖሪያ ቤታቸው በላያቸው ላይ እየተዘጋ እሳት ተለቀቀባቸው::

7.በ1970 ዓ.ም. ህወሃት በሚቆጣጠራቸው ነጻ መሬቶች ይኖሩ የነበሩ አማሮች ዘራቸው እየተቆጠሩ ተገደሉ:: ንብረታቸውም ተወረሰ:: አማራ በተገኘበት ቦታ ሁሉ እንዲገደል በይፋ አዋጅ ተላለፈ:: ብዙሃን አማራ ስለሆኑ ብቻ ተፈጁ::

8.በ1970 ዓ.ም. ኢህአፓ ከትግራይ ለቆ እንዲወጣ የህወሃት አመራር አዋጅ አስተላለፈ:: የኋላ፣ ኋላ ላይም ኢህአፓ በትግራይ ኢትዮጵያዊነት ላይና በኤርትራ ጥያቄ ላይ ያለውን አቋም እንዲለውጥ ለማስገደድ ቢሞክሩም አሻፈረኝ በማለቱ ሻዕቢያ እና ወያነ ግንባር ፈጥረው የኢህአፓን ጦር ደመሰሱ::

9.በ1970 ዓ.ም. መጀመሪያ አካባቢ በብስራት አማረ የሚመራ በቁጥር ወደ ሃምሳ ገደማ የሚሆኑ ታጋዮች ኤርትራ ውስጥ በሻዕቢያ አማካይነት የፈዳይነት ስልጠና ወስደው በተለያዩ የትግራይ አውራጃዎች ውስጥ ሰርገው በመግባት የህወሃትን እኩይ አላማ የማይደግፉ ንጹሃንን እና የመንግስት ሰራተኛ የሆኑ ሌሎች ዜጎችን በተደጋጋሚ ጥቃት ፈጁ::

10.በህዳር ወር1968 ዓ.ም. የህወሃት አመራር ከነሰራዊታቸው የግንባር ገደሊ ሃርነት ትግራይ ታጋዮችን(ይህ ድርጅት በጊዜው በግብርም ሆነ በአላማ ከህወሃት እምብዛም የማይለያይ ድርጅት ሲሆን ብዙም በትግል ሳይቆይ በህወሃት የተደመሰሰ ድርጅት ነው::) በሙሉ በጸረ ዲሞክራሲያዊ ባህሪያቸው በአንዲት ለሊት ዘገልባ ጎጥ ውስጥ በጅምላ ፈጇቸው::

11.በ1977 በትግራይየደረሰውን አስከፊ ድርቅ ተከትሎ በለጋሽ አገራት እና ህዝቦች ዘንድ ለነብስ አድንት ተብሎ የተላከውን እርጥባን የህወሃት አመራር በጥሬ ገንዘብ የመጣውን በቀጥታ ወደግል ካዝናቸው በአይነት የተለገሰውን ደግሞ በሱዳን ገበያ በመቸብቸብ ለትጥቅ መግዣ እና ለግል ሃብት አዋሉት:: እርዳታ ተላከለት የተባለው ምስኪን ህዝብም በየበረሃው ወድቆ ረገፈ:: ለመለመኛ ለታሰበ ድራማ ወደሱዳን እንዲሰደድ በህወሃት የታዘዘው ረሃብተኛም በየመንዱ ቀረ:: የትግራይ ህዝብም ታሪክ ሊረሳው የማይገባው ታላቅ ክህደት ከአብራኩ ወጣሁ በሚሉ ከሃዲዎች ተፈጸመበት::

12.በ1981 ዓ.ም. ደርግ ትግራይን ለቆ እንደወጣ ህወሃት ካለምንም ችግር በሩ የተከፈተ ቤት በማግኘቱ ሰተት ብሎ መሃል ትግራይ ገባ:: ገብቶም አላረፈም:: በየከተማው ይኖሩ የነበሩ መምህራንን እንዲሁም የመንግስት ተቀጣሪ ዜጎችን ጠላት ብሎ በደርግ ደጋፊነት በመወንጀል ለቅሞ ፈጃቸው:: ከየአውራጃው ብዙ ሰዎች መገደላቸውን በቀላሉ ማጣራት ይቻላል::

13.ህወሃት በበረሃበነበረበት ወቅት ከሻዕቢያ ጋር በነበረው (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## በወያኔው ቡድን የተፈጠረው ክፍተት እየሰፋ ነው፣ የመለስ ዜናዊ ሃውልት ተብየ በድብቅ ተመረቀ

የዘረኛውና አምባገነኑ መለስ ዜናዊ ሃውልት ተብየ ቀብሩ በተፈጸመበት በመንበረ ጸባኦት ቅድስት ስላሴ በድብቅ የተመረቀ መሆኑን ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ ባስተላለፈልን ዘገባ ገለጸ። እንደዘጋቢያችን ሪፖርት የሃውልቱ ምረቃ የተከናወነው በድብቅና አዜብ መስፍን ከነልጀቿ እንዲሁም አንዳንድ የቅርብ ዘመዶች ብቻ በተገኙበት ነው።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከሚዲያ ሽፋን መቀዝቀዝ ጀምሮ ፎቶግራፎቹ ይነሱልን፣ ሰለቹን የተባለለት ዘረኛው መለስ ዜናዊ ሃውልት ተብየ ብዙም አጀብና ግርግር ባልታየበት ሁኔታ ትናንት ማለዳ ላይ በድብቅ መመረቁ አብዛኞችን አስገርሟል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ስማቸው እንዳይጠቀስ የፈለጉና ለአገዛዙ ባለስልጣናት ቅርበት እንዳላቸው የተናገሩ ግለሰብ እንደገለጹት የመለስ ዜናዊ ሃውልት በንዲህ ያለ ሁኔታ በድብቅ መመረቁ በወያኔዎች ቡድን ምን ያህል ክፍተቱ እንደሰፋና የተከፋፈሉት ቡድኖችም ርስ በርስ ተፋጥጠው እንደሚገኙ ነው ብለዋል። እኚሁ ግለሰብ አያይዘው እንደተናገሩት መለስ ዜናዊ በሞተበት ወቅት ለአንድ ወር የዘለቀው የሃዘን ጊዜና የ 24 ሰአት ሚዲያ ሽፋን ሁኔታውና ይዘቱ በዚህ መልክ ተቀይሮ በድብቅና ኦፊሴላዊ ስነስርአትን ባልተከተለ ሁኔታ መመረቁ፣ በወያኔዎች መካከል የተፈጠረው ሽኩቻ ከቁጥጥር ውጪ መድረሱንና ሊደበቅም አለመቻሉን ነው ብለዋል።

የአምባገነኑ መለስ ዜናው ሃውልት ተብየ ምረቃ ላይ አገዛዙ በቁጥጥሩ ስር አድርጎ እንደፈለገው የሚጫወትባቸው የመገናኛ ብዙሃን ፍጹም ባልተለመደ ሁኔታ ለዘገባ አለመጋበዛቸውን ሪፖርተራችን በላከው ዘገባ አመልክቷል።

እንደዘጋቢያችን ሪፖርት በዚሁ የሃውልት ምረቃ ላይ አባይ ጸሃየ የታየ ሲሆን ከረፈደም በኋላ ቢሆን ጥቂት ባለስልጣናት በስልክ እየተደዋወሉ በቦታው መድረሳቸውን ገልጿል።

## ዘረፋ የአምባገነኑ ወያኔ አገዛዝ ባለስልጣናትና አገልጋዮቻቸው የወቅቱ ቀዳሚ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

በተለይም ዘረፋው በመከላከያ ውስጥ ጎልቶ እንደሚታይ ማስረጃዎች የሚያረጋግጡ ሲሆን የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት በሰሞኑ ዘገባው ሳሞራ የኑስ በቁራ መብራት ሀይል አካባቢ በ80 ሚሊዮን ብር ዘመናዊ ህንጻ መስራቱን በፎቶ ግራፍ አስደግፎ አቅርቧል። የሳሞራን ህንጻ ንብ ኢንተርናሽናል ባንክን ጨምሮ ሌሎች ድርጅቶችም መከራየታቸውን ለማወቅ ተችሎአል።

ይህን ቅጥ ያጣ ዝርፊያ አስመልክቶ ዘጋቢያችን ያናገራቸው አንድ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ እንደገለጹት በሃገር ሃብት ላይ ልቅና ሃላፊነት የጎደለው ዘረፋ እየተካሄደ ለመሆኑ አንዱ ማስረጃ ሳሞራ የኑስ በጎን እንዲህ አይነት ዝርፊያ ባደባባይ እየፈጸመ በሚገኝበት ሁኔታ መከላከያ ሚኒስቴር በወር 10 ሺ ዶላር የሚከፍልበት በልዩ የደህንነት መሳሪያዎች በየሚጠበቅ መኖሪያ ቤት ውስጥ የመኖሩ ጉዳይ ነው። ሳሞራ የኑስ ብቻ ሳይሆን አብዛኞቹ የህወሀት ጄኔራሎችም በቦሌ ክፍለ ከተማ በውድ ዋጋ የተገነቡ ህንጻዎች አሏቸው። እናም ኢትዮጵያዊያን ይህ ዝርፊያ፣ ግፍና በደል አንድ ቦታ ላይ እንዲቆም ካላደረግን ፍጹም ሊታጠፍ የማይቻል ጥፋት ላይ እንደርሳለን ብለዋል።

## የፋሺስት ጣሊያን ወታደሮች የኢትዮጵያን ህዝብ የጨፈጨፉበት 76ኛ አመት . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ስነስርአት ላይ ከ1928 እስከ 1933 ዓ.ም. ድረስ የፋሺስት ጣሊያን ጦር በወገኖቻችን ላይ ያደረሰዉ ጥፋት በተለያየ መልኩ የተገለጸ ሲሆን በየከተማዎቹ ላይ የተገኘዉ ብዛት ያለዉ ኢትዮጵያዊ የሙሶሊኒን ወረራ እንደ መልካም መንፈሳዊ ተልዕኮ ባርካና ቀድሳ የላከቺዉ ቫቲካን የኢትዮጵያን ህዝብ ይቅርታ እንድትጠይቅ፤የጣሊያን መስግስት ኢትዮጵያ ዉስጥ ፋሺስቶች ላደረሱት በደል ተመጣጣኝ ካሳ እንዲከፍል፤በቫቲካንና በጣሊያን መንግስት የተዘረፉ ንብረቶች እንዲመለሱና በተለይ በቅርቡ አፊሌ በምትባል የጣሊያን ከተማ ዉስጥ የተገነባዉ የፋሺስቱና የጦር ወንጀለኛዉ የማርሻል ግራዚያኒ መታሰቢያ እንዲፈርስ ጥያቄ አቅርቧል። ከዚህ በተጨማሪ በየዓመቱ ዉስጥ ለ1928ቱ ሰማዕታት ፀሎት የተደረገ ሲሆን የየዓመቱ አባቶች የፋሺስት ጣሊያን ጦር በሠላማዊ ኢትዮጰያዉያን ላይ የፈጸመዉን ግፍ በዝርዝር ተናግረዋል።

## የህወሃት መሪዎች "የኢትዮጵያ ታሪክ እንደገና መፃፍ አለበት!" ይላሉ:: ለምን?? . . . (ከገጽ 3 የዞረ)

ኢትዮጵያን እና ኢትዮጵያውያንን የማጥቃት የጋራ ውል የትግራይ ወጣት ሴት እና ወንዶችን ሻዕቢያን ለማጠናከር በተለያዩ ጊዜያት በባርነት አሳልፎ ይሰጥ እንደነበር የሚታወቅ ሃቅ ነው። ይህም የትግራይን ልጆች ወደማያውቁት ጦርነት አሳልፎ የመማገድ ዘመቻ ይፈጸም የነበረው በአስገዳጅነት እንደነበር እሙን ነው። ከ1969-1970 ዓ.ም. ብቻ በቁጥር ወደ 29,000 የሚገመቱ የትግራይ ወጣቶችን ለሻዕቢያ አላማ ማስፈጸሚያ አሳልፎ ሰጥቷል። የቀይ ኮከብ ዘመቻ እንደተጀመረ የህወሃት አመራር ከዚህ በፊት ያደረገው ሳይበቃው ከ1971-1974 ዓ.ም. ተጨማሪ በቁጥር ወደ 70,000 የሚደርሱ የትግራይ ልጆችን በደርግ ጥቃት የውድቀት ገደል ላይ የደረሰውን ሻዕቢያን ለማዳን በቀጥታ በሻዕቢያ እዝ ስር አዘመተ።ይህም ሳይበቃው ቀይ ኮከብ ዘመቻ በተፋፋመበት ወቅት በ8 ብርጌድ የተደራጁ በቁጥር 13,500 የሚደርሱ ተጨማሪ የትግራይ ወጣቶችን ለሻዕቢያ ህልውና ማስጠበቂያነት ለጭዳነት ላከ። እነዚህ ሁሉ በማያውቁት እና ይልቁንም አገራቸውን ለሚጎዳ ጦርነት በባንዳነት ህወሃት አሰልፎ የላካቸው የትግራይ ወጣቶች ደም በየበረሃው መና ሆኖ ቀረ። በጠቅላላው ህወሃት ለወሬ ነጋሪነት እንኳን ያልተመለሱ በቁጥር ከ112,500በላይ የትግራይ ልጆችን ለሻዕቢያ ጦርነት ማጠናከሪያ እንደላከ ማስረጃ አለ። አንዳንዶችም ቁጥሩ ከዚህ ሊልቅ እንደሚችል የሚናገሩ አሉ። ይህ ነው እንግዲህ ትግራይን ነጻ አወጣለሁ የሚለን የነ ስብሓት እና መለስ ጉጅሌ የተሸከመው እና እንዲሰማ የማይፈልገው ጥቁር ታሪክ።

14. በ1981 ዓ.ም. የአሜሪካ መንግስት ተወካዮች በየካቲት ወር በሱዳን ካርቱም መለስ ዜናዊ እና ኢሳያስ አፈወርቂን አነጋግረው እንደምን ስልጣን እና አገሪቷን ከደርግ ውድቀት በኋላ እንደሚያስተዳድሩ አደላድለው ሲያበቁ ለወያነ ከሃዲዎች ኢትዮጵያን አመቻችተው አሳልፈው ሰጧት።
15. ከደርግ መዳከምጋር ተያይዞ የአገሪቷ አራቱም ማዕዘናት ክፍት በመሆናቸው ህወሃት ከመቀሌ ተነስቶ ካለምንም ችግር አዲስ አበባ ሊገባ ቻለ። ከሽሬ ተነስቶ በጎንደር፣ በባህርዳር በኩል አድርጎ አዲስ አበባን ተቆጣጠረ።

ህወሃት ኢትዮጵያን ወሮ አዲስ አበባ ከገባ በኋላ የመንግስትን ስልጣን ተቆጣጥሮ የሰራውን ወንጀል በዝርዝር ለማቅረብ ይሄ ጽሁፍ ብቻ በቂ አይደለም። ስፍር ቁጥር የሌለው የአገር ክህደት እና የዘር ማጥፋት ስራዎች በተለያዩ ቦታዎች በሚኖሩ ንጹሃን ኢትዮጵያውያን ላይ ፈጽሟል። በተለያዩ ቦታዎች በአማራዎች ላይ ፣ በጋምቤላ በአኝዋኮች ላይ ፣ በአዋሳ በሲዳማዎች ፣ በኦጋዴን በኢትዮጵያ ሶማሌዎች ላይ እንዲሁም በመላ አገሪቱ ባሉ እስር ቤቶችን ታጉረው በሚማቀቁ በ10,000 የሚቆጠሩ ኦሮሞዎች ላይ እስከ ዘር ማጥፋት(genocide) ደረጃ የሚደርስ ወንጀል ፈጽሟል።አሁንም እየፈጸመ ነው።
በተለያዩ የመረጃ ምንጮች እንደተገለጸው ህወሃት በበረሃ በነበረበት ወቅት በአሜሪካን መንግስት በሽብር ድርጊቱ እንደ አል ቃኢዳ አሸባሪ ድርጅት ተደርጎ ይታይ እንደነበር ወጣቱ ጋዜጠኛ አበበ ገላይ ከግሎባል ቴረሪዝም ዳታ ቤዝ (Global Terrorism Database) ላይ አሳይቶናል። ይህንን መረጃ ማየት ለሚፈልግም ሰው ከኢንተርኔት ላይ ማግኘት ይችላል።

የህወሃት ጥቁር ታሪክ እንግዲህ ይህ ነው። የእነ መለስ ዜናዊ ፖለቲካ እና አመራር በበረሃም ሆነ በከተማ ይህ ነበር።ታሪክ ዳቦ ሆኖ አንበላውም ከሚል እጅግ አሳናፊ እና መሰሪ ትንተና ጀምሮ የኢትዮጵያን ታሪክ የማንቋሸሽ እና የማጨማለቅ ስራ የህወሃት ዋንኛ የፕሮፖጋንዳ ግብ እንደነበር እና አሁንም እንደሆነ ከአፋቸው የሚወጣውን ንግግር በመስማት መገንዘብ ይቻላል። እነኘህ ናቸው እንግዲህ አማራን እና ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን እናጠፋለን ከሚል ጀምሮ ኢትዮጵያን አፍርሰን እንሰራለን እና ታሪኳንም እንደ አዲስ እንጽፋለን የሚሉን።

የስርዓቱ ዋና አንቀሳቃሽ መለስ ዜናዊ በሞት ተቀስፎ ከሄደ እነሆ ወራት ተቆጠሩ። ሊታረቅ በማይችል የክህደት ቁልቁለት ውስጥ ያለው ህወሃትም ፍጹም ሊመልሳቸው በማይችላቸው ታሪካዊ ጥያቄዎች ተወጥሮ የውጪ ነብስ ፣ ግቢ ነብስ ግብግብ ላይ ይገኛል። የድርጅቱ እኩይ አላማ እና ግቡ ዛሬ ፍንትው ብሎ በወጣበት ወቅት ላይ ኢትዮጵያውያን በመላ ኦሮሞ ፣ አማራ ፣ ትግሬ ፣ እስላም ፣ ክርስቲያን ሳይሉና አላስፈላጊ አተካራቸውን ወደጎን በማለት ይህንን የታሪክ አሽከላ የሆነ ዘረኛ ቡድን ከስረ መሰረቱ ነቅለው መጣያ ጊዜው አሁን ነው። በስቃይ ያሉ ወገኖቻችንን እና አገራችንን ከወያኔ መንጋጋ እናላቅ። የሀገራችንን እና ህዝባችንን በጎ ታሪክ እና መጻኢ እድልም እናስመልስ።

ገብረመድህን አርአያ
የካቲት 2005

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

መካከኛ ሞገድ:- በ 358 MB, በ 837 kHz
አጭር ሞገድ:- በ 31 MB በ 9700 KHz
በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz
በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሚም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቄያችን አድራሻዎች እንድታሳውቁን እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org